City of Seattle

# ተከራዮችን ከቤት ማስወጣትን በጊዜያዊነት ስለማቆም

እስከ ጁን 4 ወይም የሲቪል አስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌው ከቀጠለ፣ ከዛም ለረዘመ ጊዜ ዋሽንግተን ውስጥ የሚገኙ የመኖሪያ ቤት ነዋሪዎችን ከቤት ማስወጣት ቢጊዜያዊነት የታገደ ሲሆን፣ ይህም ሃገረ ገዥው Inslee በ COVID-19 ምክንያት በሰጡት ትእዛዝ መሰረት ነው።

## አሁንም የኪራይ ክፍያ መክፈል አለብኝ?

*አዎ።* ነገር ግን፣ በ COVID-19 ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖ ምክንያት ኪራይዎን ለመክፈል ካልቻሉ፣ አከራይዎ ባለው ነባራዊ ሁኔታ መሰረት የክፍያ ዕቅድ ለማዘጋጀት ከእርስዎ ጋር በትብብር መስራት አለባቸው።

## አከራዬ የቤት ኪራዬን ዋጋ መጨመር ይችላሉ?

የለም፣ ጊዜያዊ እገዳው በስራ ላይ እያለ አከራይዎ የኪራይ ዋጋ ወይም የዋስትና ተቀማጭ ገንዘብን መጨመር አይችሉም።

## የቤት ኪራዬን በወቅቱ ባለመክፈሌ ተጨማሪ ክፍያ ልከፍል ይገባኛል?

የለም። ጊዜያዊ እገዳ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ ውስጥ ለዘገየ ክፍያ ተጨማሪ ማስከፈል አይፈቀድም። አከራይዎ በዕዳ መሰብሰቢያ ዘዴ አማካይነት ውዝፍ ኪራይ መሰብሰብ ወይም ይህን ለማድረግ ማስጠንቀቂያ መስጠት አይችልም።

## ከአከራዬ ጋር ስለጉዳዩ መነጋገር እችላለሁ?

አዎ! ከአከራይዎ ጋር ያለዎትን የግንኙነት መስመር ክፍት ያድርጉ። አከራይዎም የኪራይ ክፍያ አለመቀበል ስለሚያደርስበት ተጽእኖ አስቀድሞ ማቀድ ይኖርበታል።

## ጊዜያዊ እገዳ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ ውስጥ ከቤቴ ልባረር እችላለሁ?

እርስዎ ለጎረቤቶችዎ እና/ወይም ለአከራይዎ ጤናና ደህንነት የቅርብ ስጋት የሚጋርጡ ከሆኑ ብቻ።

## በጊዜያዊ እገዳው ወቅት የ14 ቀናት ክፈል ወይም ልቀቅ ማስታወቂያ ወይም ሌላ ከቤት ማስለቀቂያ ማስታወቂያ ቢደርሰኝ፣ እገዛ ከየት ማግኘት እችላለሁ?

በስልክ ቁጥር(206) 684-5700 ደውለው ለ Renting in Seattle የስልክ መስመር ያሳውቁ ወይም ቅሬታዎን ኦንላይን ያቅርቡ https://cosaccela.seattle.gov (+Create New የሚለው ስር ፈልገው Complaint የሚለውን ይምረጡ)። የቋንቋ እገዛ ይቀርባል።

በጣም የቅርብ ጊዜ መረጃን ለማግኘት፣ ይህን ይጎብኙ፡- seattle.gov/rentinginseattle
በስልክ ቁጥር 206.684.5700 ይደውሉልን

## ተጨማሪ የ COVID-19 የመረጃ ምንጮች

የኮሙኒቲ የመረጃ ምንጮችን ለማግኘት፡- www.seattle.gov/mayor/covid-19
የፋይናንስ እገዛና መሰረታዊ ፍላጎቶችን ለተመለከቱ መረጃዎች 2-1-1
የስራ አጥ ኢንሹራንስ መረጃን በተመለከተ፡- https://esd.wa.gov/newsroom/covid-19